# እናት ባንክ አ.ማ
# ENAT BANK S.C.

## የባለአክሲዮኖች 4ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የስብሰባ ጥሪ

የእናት ባንክ አ.ማ የባለአክሲዮኖች 4ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ቅዳሜ ህዳር 16 ቀን 2010 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ በሚሊኒየም አዳራሽ ይካሄዳል፡፡
ስለሆነም የባንኩ ባለአክሲዮኖች በአካል ወይም በሕጋዊ ተወካዮቻችሁ አማካኝነት በተጠቀሰው ቀን'ቦታና ሰዓት በጉባኤው ላይ እንድትገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ በአክብሮት ጥሪውን ያቀርባል፡፡

### የ4ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

1. የጉባኤውን አጀንዳ ማጽደቅ፤
2. የአዳዲስ አክሲዮኖች ግዢና የተደረጉ የአክሲዮን ዝውውሮችን ማሳወቅ፤
3. የባንኩን የዲሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ማዳመጥ ፤
4. የውጪ ኦዲተሮችን ሪፖርት ፤ የሀብትና ዕዳ ሚዛን እና የትርፍና ኪሣራ መግለጫ ማዳመጥ፤
5. በተራ.ቁ. 3 እና 4 በቀረቡት ሪፖርቶች ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ፤
6. እ.ኤ.አ. በ2016/2017 በጀት አመት የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት ተወያይቶ ማጽደቅ፤
7. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ወርሃዊ የትራንስፖርት አበልና የአገልግሎት ክፍያ መወሰን፤
8. የውጪ ኦዲተሮችን መምረጥና ክፍያቸውን መወሰን፤
9. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ ሪፖርትን ማዳመጥ፤
10. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ምርጫ ማከናወን፤
11. የጉባኤውን ቃለጉባኤ ማጽደቅ፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

በጉባኤው ላይ በአካል መገኘት ለማትችሉ ባለአክሲዮኖች ከስብሰባው ዕለት ሶስት ቀናት በፊት ዮርዳኖስ ሆቴል ፊት ለፊት እናት ታወር ላይ በሚገኘው የባንኩ ዋና መ/ቤት 1ኛ ፎቅ ፋይናንስና አካውንትስ መምሪያ በመቅረብ ባንኩ ባዘጋጀው የውክልና ቅጽ ላይ በመሙላት ተወካዮቻችሁን ማሳተፍ ትችላላችሁ፡፡ ወይም ተወካዮቻችሁ አግባብ ካለው የፌዴራል ወይም የክልል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተሰጠ በስብሰባ ለመሳተፍና ድምፅ ለመስጠት የሚያስችል የውክልና ሰነድ ዋናውንና ፎቶ ኮፒውን ይዘው በመቅረብ መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እናስታውቃለን፡፡
ባለአክሲዮኖችም ሆናችሁ ወኪሎች ወደ ስብሰባው ቦታ ስትመጡ ኢትዮጵያዊነታችሁን የሚያረጋግጥ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ይዛችሁ እንድትቀርቡ፡፡ እንዲሁም ተወካዮች የወካያችሁን ዜግነት የሚያረጋግጥ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ በተጨማሪ ይዛችሁ እንድትቀርቡ እናሳስባለን፡፡

**የእናት ባንክ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ!!!**